የብዙዎች አንደበት በተዘጋበት ፤ ፍርሀትና ልቅሶ በሰፈነበት ዘመን ብዕሩን በማቅናት ያንን ቀውጢ ግዜ በብዕሩ የዳሰሰ ኢትዮጵያዊ ጸሀፊ ቢኖር በዓሉ ግርማ ነው። ይህ ብዕር የዶለዶመው አንደበቱም የተዘጋው ሀሙስ የካቲት 24/1976 ዓ/ም ከቀኑ 11:30 ከቤቱ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ቤተሰቦቹን ማየት ሲሳነው ሲሆን። ህይወቱ እንደ ብዕሩ ዛሬም ሚስጥር ሆናለች። በጊዜው የነበረው መነግስት እጁ እንደሌለበት ለማሰተባበል የማፈላለጉ ስራ እንዲቀጠል ለይስሙላ ቢያዝም ከመንግስት የተደረገ ምንም ጥረት አልነበረም። በቤተሰቦቹ ክትትል በእለቱ ይነዳው የነበረው መኪና በደብረዘይት መንገድ ቆሞ የተገኘ ሲሆን ይህን እውቅ ፀሀፊ ምን እንድበላው ዛሬም መልስ አለተገኘም። ከመጥፋቱ ሰባት ወራት በፊት ከየመደርደርያው እየተለቀመ የተማገደው የደራሲው መጽሀፍ ፤ ከማስታወቂያ ሚኒስተር ስራው ተገልሎ እቤት እንዲቀይ መደረጉ ። አበዮቱን መንጋጋ ውስጥ እኮነው የከተከተው የሚለውን ቅሬታ ከኮኔሬል መንግስቱ መስማቱ የመሰወሩን ሚስጥር ግልጽ ያደርገዋለ።

በዓሉ መስከረም 10/1931 ዓ/ም በኢሊባቡር ክፈለሀገር ክህንዳዊው አባቱ ና በወቀቱ ሀበታም ከነበሩ ቤተሰቦች ከተወለዱ እናቱ ወ/ሮ ያደኔ ቲባ በኢሊባቡር ጠቅላይ ግዛት ሱጪ ቦሩ በምትባል አነስተኛ የገጠር መንደር የተወለደ ሶሆን አባቱ ቤተሰባቸውን ወደ አዲስ አበባ ለማዛወር ሞክረው የእናቱ ቤተሰቦች ባለመስማማታቸው ከእናቱ ጋር ኢልባቡር እንዲቀር ከአባቱም ጋር የጠበቀ ገንኙነት አንዳይኖረው ሆኗል። በኢልባቡር ከአያቱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደነበረውና በጊዜው ስለነበሩት ምምህሩ በተደጋጋሚ ከማውራት ሌላ ስለ ኢሊባቡር ህይወቱ ብዙም አያወራም ነበር። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን እዚያው በትውልድ ሀገሩ ሱጪ ከአጠናቀቀ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመመጣት በልዕለት ዘነበወርቅ ትምህርትቤት ትምህርቱን መከታተል ጀመረ በጊዜው በሚሰጠው ፈተና ክፍተኛ ውጤት በማግኘቱ በ1943 ዓ/ም ጀነራል ዊንጌት ትምህርትቤት የመግባት ዕድል ለማግኘት ችሏል። በጀነራል ዊንጌት በጎበዝ ተማሪነቱ ፤ ተማሪዎችን ለአመጽ በማነሰሳት ችሎታው ሲታወቅ ስነጽሁፍን የሀይወት መርህ ለማድረግ የመጀመሪያውን ጥሪ የተቀበለበት ግዜ እንደሆነ ይነገራል። በአዲስ አበባ በነበረበት ግዜ አንደወላጅ የተንከባከቡትን የቅርብ ቤተሰብ ስም በመውስድ በዓሉ ግርማ በሚለው መጠሪያ ይጠራ የጀመረው የኮሌጅ ተማሪ ሆኖ ነበር።

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

በዓሉ ግርማ በ1954 ዓ/ም ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በፖለቲካ ሳይንስና በጆርናሊዝም የመጀመርያ ድግሪውን ሲያገኝ በትምህርት ላይ እያለ ለኢትዮጲያ ሄራለድ ጋዜጣ በሪፖርተርነት እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በጊዜው ይታተም ለነበረው NEWS and VIEWS ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆኖ ሲያገለግል የንጉሱን ሥርዓት የሚነቅፉ ጽሁፎችን በማቅረቡ ከመንግስት የተሰወረባቸው ግዚያት ነበሩ። ትምህርቱን እንደጨረሰ የስኮላርሽብ እድል በማግኘቱ በፖለቲካ ሳይንስ ና ጆርናሊዝም የማስተርስ ዲግሪውን East Lansing Michigan ከሚገኘው በርክሊ ዩንቨርስቲ አግኝታል።

በስራ ዓለም

በ1955 የዛሬይቱ ኢትዮጲያ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ

በ1957 የመነነና የአዲስ ሪፖርት ምፅሄቶች ዋና አዘጋጅ

በ1960 የኢትዮጲያን ሄራለድ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ

ከ1962 – 1966 በጋዜጣው ህይወት ታሪክ ለመጀመርያና ለመጨረሻ ግዜ ታማኝነት ባገኘው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ

በ1969 የማስታወቂያ ሚኒስተር ቋሚ ተጠሪ ሆኖ ሲያገለገል በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተጋባዝ መምህር በመሆን በ creative writing ሙያ በርከት ያሉ ባለሙያዎችን ለማፍራት ችሏል። በስራ ዓለም ተግባቢ ና ሰርቶ ማሰራት የሚችል ፤ በሙያው የተመሰገነ እንደነበረ አብረውት የሰሩት ይናገራሉ። ጋዜጦች ላይ በሚያቀርቡ ጸሁፎች የተናሳ የደሞዝ መቆረጥ ና ከስራ መባርር የመሰሉ ችግሮችም ደርሰውበታል።

ታዋቂው ጸሀፊ ስብሀት ገ/እግዛብሄር በዓሉ ገፀባህሬዎቹን ከእግዛብሄር ይረክብና ኑሮቸውን መጽሀፉ ውስጥ ያድርገዋል ይላል ፤ በርካታ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች በበአሉ ስንጽሁፍ ዙሪያ የመመረቂያ ጥናታዊ ጽሁፍ ሰርተዋል። በርካታ ምሁራኖች ዘመናዊ ጸሀፊነቱንና ለሀቅ ሟች መሆኑን አስምረውበታል።

በዓሉ ግርማ በህይወት ዘመኑ በ1962 ዓ/ም ከአድማስ ባሻገርን በ1966ዓ/ም የህሊና ደውልን በ1972 ዓም የቀይ ኮኮብ ጥሪን ና ደራሲውን በ1975ዓም ሀዲስንና ኦሮማይን እንዲሁም በየካቲት በሚለው የማስታወቂያ ሚኒስተር ወርሀዊ መጽሄት ላይ የፍጻሜ መጀመሪያ የሚል ልብወልድ መጣጥፍ አቅርቧል። የበዓሉ የስንጽሁፍ ስራዎች

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

1 የክርስቶስን የስብዕና ገጽታዎች በተወሰኑ መልኩ የሚያንጸባርቁ ፤ ዘላለማዊነት ያላቸው ገፀባህርያት በመጸሀፉ ውስጥ ይታያሉ ገፀባህሪዎቹ ለሰው ልጆች አዛኝነት ርህሩርህነትን የሚያሳዩ ናቸው።

2 እራስን መገምገም ፤ተግባር ማከናወን፤ ውጤታማ ሆኖ መገኘት ፤ወቅታዊ ማህበራዊ ና ፖለቲካዊ ችግሮችን ማንፀባረቅ የመጽሀፎቹ ተልኮች ናቸው።

3 ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር የሚዛመዱ ፤ በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረቱ ፤ ታሪካዊነት ፤ ደፍርት ያላቸው ገፀባህርያትን ያዘሉ ሲሆኑ አፃፃፉ ፍቅርን፤ ሴራን ፤ ወሲበን አስታኮ የመተረክ ዘዴ ይታይበታል።

4 አንባቢያን ከገፀ ባህርያቱ ጋር በፍቅር እንዲወድቁ ፤ ከዕለት ተዕለት ኑራችን ጋር የሚመሳሰል ትዝታን የመፍጠር ችሎታ ያላቸው ገጸ ባህርያት የታየሉ

5 በየጊዜው የነበሩ ግራ አዝማሚያዎችን ፤ ከውጪ የሚመጡ አሰተሳሰቦች ለኢትዮጲያ እንደ ማያስፈልጓት ፤ የግለሰብ ነፃነትን አስፈላጊነተን አጥብቆ ይከራከራል።

6 በጋዜጠኞች ፤በጻሀፊያን የሚደርሰውን ተጽዕኖን በማጋለጥ የፕሬስ ነፃነት አሰፈላጊነትን አጉለቶ ያሳያል።

7 በሴት እህቶቻችን ላይ የሚደርሰውን በደል ፤ ማህበረሰቡ ለሴቶች ያለውን የተዛባ አዝማሚያ የሴቶች እኩለነትና የባህል ታህድሶ አስፈላጊነት አጥብቆ በመከራከር በሁሉም መጽሀፎች የዋና ገጸባህረተያቱ ታሪክ በማድርግ ችግሩ ጎልቶ እንዲወጣ ታለቅ ተዋጾ አበርክቷል በአድማስ በሻገር ሉሊት፤ በህሊና ደውል ሽታዮ፤በደራሲው ዕጌ፤ የቀይኮከብ ጥሬ ፍኖት እነዲሁም በኦሮማይ ፍያሜታ ክብረ ንፅህናቸው በሀይል የተገፈፉ በደረሰባቸው በድል ምክንያት ህይወታቸው ከሀዲድ እንደወጣ በማሳይት ማህበረሰቡን ለማስተማር ችሏል።

8- በአብዮቱ ወቅት የታዩትን ኢሰባዊ ድርጊቶች በማመዝግብ በወቅቱ ለመህበረሰቡ ያቀረቡ ፤ በታሪክነታቸው ፤ በትምህርትነታቸው ለማሰቀምጥ የቻሉ ታሪካዊ ስራዎች ናቸው።

ከእድማስ ባሻገር

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

የመጀመሪያው የደራሲ በዓሉ ግርማ የህትማት ሥራ ሲሆን ስምንት ግዜ ታተሞ ለመሸጥ ሲችል።እራሱን አንድ ቀን ለመግለጽ በሚዋትተው በዋናው ገፀባህሬ አበራ ወርቁ ፤ ከውስጡ ያለውን ብርሀን ለማየት እንዲችል አበራን በሚጎተጉተው ሀይለማሪያም እንዲሁም በዘራቸው በማንነታቸው የሚኮሩት ይሁነ እንጂ የሚፈልጉትን ካዲሱ ትውልድ
በሚያውቁት ወንደሙ አቶ አባተ ገፀባህርያት ላይ ያነጣጠረውና በጊዜው የነበረው ወጣት ምሁር እራሱን ለትልቅ ሀላፊንት ያጨ ቢሆንም ከወላጆች ፤ ከመንግስት ትከሻ ላይ ተንጠልጥሎ ከመውሰድ በስተቀር መልሶ የተካው ምንም እንደሌለ ትውልዱ ያለበትን ችግር ጠነቅቆ የማያውቅ ችሎታውንና ህልሙን ያለፈተነ መሆኑን ። የወደፊቱን ባለቅኔ ፤ ደራሲ ፤ ሰዓሊ ፤ የጥብብ ጎህ ቀዳጅ ሊሆን የሚችል ትውልድ ሀላፊነቱን ሊወጣ ያልቻለበት ምክንያቶች ከምሁሩ ፤ ምሁሩን ካፈራው ማህበረሰብ ፤ ወይስ ምሁሩ አልፈው ከመጣው ተቋም በማለት በውቅቱ ሀገሪቱ ያፈራቻቸው ምሁራን አቅጣጫ ሊመረመር እንደሚገባው አጽንቶ ይከራከራል።

" በጢት መጥቼ በዚህ ወንበር ላይ ስጎለት ራሴን የምመለከተው የበሰበሰ እንቁላል ላይ የተቀመጠች ዶሮ አድርጌ ነው የምቆጥረው ነገር ግን ግማቱ አይሰማኝም። " በማለት የሚናገረው አባራ የደራሲ ባዓሉን መጽሀፍ ወና መልክት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

የህሊና ደውል

የኢትዮጲያ ሰረየት የሚሰራ እጅ ነው ። በባድ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ መሻሻል ትርጉም አይኖረውም በማለት በኢሊባቡር መቱ አቅራቢያ የምትገኘውን የሱጺ በሮን ከተማ መልካ ምድር ፤ በ1966 ዓም የታየውን ድርቅ ፤ በማህበረሰቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ይታይ የነበረውን የከፋ ህይወት እየተረከ ህይወቱን ፤ ፍላጎቱን ና የዘመኑን ትውልድ ፍልስፍና በመተው በውቅቱ የዩንቨርስቲ ትምህርቱን አቋርጦ ትምህርት የህብረተሰቡ ጉዳይ ነው በህብረተሰቡ የሚካሄዱ ትምህርት ቤቶች ናቸው የሚያስፈልጉት በማለት ትምህርት ቤት ለመስራት ሀዋርያ ስለ ሆነው መምህር አዲስ የሚተርከው የህሊና ደውል በጊዜው ይታይ የነበረውን ፖለቲካዊ ውዝንብር በግልጽ በማጋለጥ ሀገሪቱን አስተሳስሮ ያቆየው ገመድ እየመነመነ መሄዱን ይህን ገመድ እንደገና ለማጠናከር ከባዳን የፖለቲካ ፍልስፍና ፤ከጥቂት ሰዋች ጥቅምና ፍላጎት ፤ ከጎሳና ከሀይማኖት በላይ ከኢትዮጲያን ባህሬ ልምድ፤ ባህልና ኑሮ የመነጨ ተነጥሮ የወጣ የፖለቲካ ፍልስፍና አይዲዮለጂ መመስረት አለበት ብሎ በአጽኖት የሚከራከር ሲሆን ሀገሪቱም ለውጥ እንደሚያስፈልጋት የለውጥ ህግ

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ከተገደበ ወድ ኩሬነት ተለውጦ ጤናማ አይሆንም የሚለውን የባዓሉን ብዕር ዛሬ ዞር ብሎ ላጤነውየጻሀፊውን ብስልት መለካት ይችላል። ይህ መጽሀፍ ግለሰቦች በማህብረሰቡ ውስጥ የሚጫወቱት ሚና መልካም ነገር ለመስራት ምን ያህል አስተዋጾ እንዳለው መምህር አዲስና ፊታውራሪ ተካ የነበረወን ችግር ሁሉ ተቋቁመው ለሱጺ በሮን ህጻናት ትምህርት ቤት መስራታቸው ይቸላል የሚለውን የዘመኑን አባባል በዓሉ ቀደም ብሎ እንደገለጸው እንድናጤን ያደርገናል ። በዚህ መጽሀፍ አብዛኞቹ ገፀባህርያቱ/ የፍቅረ ሰባኪዋች ሲሆኑ ደራሲው ሰዋች ከዓላማችው ጋር በፍቅር ሲወድቁ ህይወት የተለየ ትርጉም እንደሚኖራት በሚቀጥለው ሁኔታ ገልፆታል።

‶ ያለፍቅር ህይወት ትርጉም የላትም ህልውናዋ ባዶ ፤ የሚጮህ ናሳ ወይም የሚንሿሿል ፀናጽል ትሆናለች ያለፍቅር ብሔራዊ አንድነት ትርጉም የለውም ፍቅር እግዜር ነው። ፍቅር ከልባችን በሚመነጭበት ወቅት እያንዳንዳችን እግዜር እንሆናለን ፍቅር እግዛብሔር ነው። ″

የቀይ ኮከብ ጥሪ

የፊውዳሉ ስርዕት ቅሪት በሆኑት በፊታውራሪ ጉልላትና በባለቤታቸው ወሮ አምሳለ በኢህአፓ አባላት ልጆቻቸው በሂሩትና ተሰማ የጊዜው ሁኔታ ጭራሽ ባልጣመው ጋዜጠኛውና ቢሮክራቱ የወ/ሮ እምሳለ ወንድም ጌታቸው በፊታውራሪ ቤት ባደገውና የቀይ ኮከብ ጥሪ በተቀበለው ደርቤ ታሪክ ዙሪያ በጊዜው የነበረውን የማህበረሰቡን ምስቅልቅል አመለካከት ልዩነት በማውሳት የሚተርክው የቀይ ኮከብ ጥሪ የበዓሉ የድህረ አብዮት የበኩር ልጅ ሲሆን በቀይ ሽብር ዘመን የነበረውን ቀውጢ ህይወት ቁልጭ አድርጎ ያስቀመጠ ነው። ግዜው ምቀኝነት የግል ፍላጎትን በመድብ ትግሉ እያስታከኩ የሚያወናብዱበት እንደነበረ በጊዜው የውይይት ክበብ አባሎች ስራውንም ስልጣኑንም በመያዝ ሀገሪቱን ወደ ማትወጣበት ችግር እንደከተቱ የቀበሌ አብዮት ጥበቃዎች ፍርዱን በእጃቸው በመያዝ ኢድህ ፤ አናርኪስት በማለት ብዙ እናቶችን ፤ እህቶችን ደፍረው ፤ አይናቸው አወጥተው ፤ ጡታቸውን ቆርጠው፤ የህዝቡን ልጆች ካለርህራሄ አስቃይተው የኢህፓን ጋዜጣ እያስታቀፉ በየመንገዱ እንደሚወረውሩ። በተለይ በመዲናዋሀአዲስ አበባ የሰላም እንቅልፍ የሚተኙ የታደሉባት ሀዘን የወረሳት ከተማ እንደነበረች ቀይ ሽብር የተፋፋመበት ሬሳ በየመንገዱ ዳር ወድቆ ሲታይ ልጆቸቸው የጠፋባቸው ቤተሰቦች ሬሳ በማገላበጥ ለጆቻቸውን ሲፈልጉ መሰተዎሉን ፤ ወታደሮች በቀሚ ተጠሪ በመባለው

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ጂፓቸው በመሆን በአዲስ አበባን ህዝብ ላይ ፍርሀት ማንገሰቸውን ያተተ ታሪካዊ መጽሀፍ ነው።

በወቅቱ በሀገሪቱን በበቀሉት የተላያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች መክንያት የተፈጠረው ሽኩቻ ተራ ግድያን በመፍጠር በሀገሪቱ ላይ የማየጠፋ እሳት መጫሩን የፖለቲካ ድርጀቶች የወጣቱን ጠንካራ መንፈስና ድርጅታዊ ዲሲፒሊን ለሀገር በማይጠቅም ርዮተዓለም ከማበከን በሀገር ላይ እንዲውል ቢያደርጉት ስንት መልካም ስራ ሊሰራ እንደሚችል እያተተ በጊዘው የነበረው ህይወት የደንቁርን ዓለም እንደነበር መጽሀፉ ያመላክታል።

ሀዲስ

በህሊና ደውል የኢትዮጰያ ስሬት የሚሰራ እጅ ነው በማለት የተግባር ህይወቱን ያሳየው ሀዲስን በዓሉ ግርማ በጣም በሚጥም ያጻጻፍ ስልትና ለአንባቢ በሚቀልና አቀራረብ ተንታኝ በሆነ መልኩ እዲስ በሚለው መፅሀፉ ህየወቱን የብዙሀን ወኪል አድርጎ እንዲታይ አድርጎታል ። ሀዲስ ስራ ለመፈለግ በሚያደርገው ጥረት፤ ምልካም ነገር ለመስራት ሲፍጨረጨር ከቢሮክራሲ ጋር የሚያደርገው እሰጣ ገባ ፤ግልፅ፤ የዋህና ደፋርነቱ የአንባቢያንን አይን የሚስብና በዓይነ ህሊናችን ብዙ ሀዲሶችን እንድንቃኝ ያደርገናል።የትምህርት ዓላማ መሆን ያለበት ትምህርትን ማዳረስ ሳይሆን ሀገሪቱን ሊመሩ የሚችሉ ጥቂት ጥራት ያላቸው ምሁራንን ማፍራት ነው ። ህሊና ህይማኖት የሚለት ዝባዝንኬዎች ለእድገት ጠንቅ ናቸው ።ማህበራዊ ሀበት ክፍፍል ሶሻሊስታዊ አስተያየት ነው በማለት በድርጊቱም ሆነ ባስተሳሰቡ ከሀዲስ የተላየው ታፈስና ሀዲስ የሚያደርጉት የወቅቱ የሀሳብ ልዩነት በውቅቱ ብቅብቅ ያለው ካፒታላዊ ስረአት አቀንቀኝ ክፍል የነበረውን የተሳሳተና ከሀገሪቱ ሁኔታ ጋር የማይሄድ አሰተሳሰብ ቀልጥ አድረጎ የሚሳይ አቀራረብ ነው።

ደራሲው

የደራሲያንና የተደራሲያንን ሙግት በሰፊው የሚታይበት ሲሆን ደራሲው እውነተኛ ደራሲ ለመሆን ያለውን ጥብቅ ፍላጎት

" ከምፈጥረው ገፀ ባህርያት አጥብቄ የምጠብቀው ማህበራዊ ድፍረት፤ ትህትና ፤ ፍቅር ፤ ሀቀኝነት፤ ቀጥተኛ መሰዋትነት በእኔ ባህሬ ውስጥ የት አለ ?"

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

" መጻፍ አልቻልኩም ሀቁ ይህ አይደለም ሀቁን ክእራሴ እደብቀዋለው ፤ መጻፍ አልቻልኩም ጊዜዬን በከንቱ ነው የማጠፋው የምለው ነገር የለኝም ቢናረኝም ምን እንደሆነ አላውቅም ባውቅም በቃላት ልገልጸው አልቻልኩም ቃላት መግለፅ ያለባቸውን አይገልፁም ያሾፋሉ። " እያለ ከእራሱ ጋር የከፈተው ጦርነት ዘመኑ ምን ያህል የፍርሀት ዘመን እንደነበር የሚያሳይ ሲሆን በወቅቱ በሀገሪቱ ወስጥ የነበረውን ፖለቲካዊ ቅራኔ

" ሱሪ ባንገት አውልቅ ምርት! ምርት! አረነጓዴ ዘመቻ ውይይት ክብብ፤ ውግዘት ፤እርግማን፤ መኮነን፤መጠቆም ፤ ማጋለጥ ፤ መዋጮ ለእናት ሀገር ጥሪ ፤ ለመልሶ ማቋቋም " በሚመስል አገላለጽ የገለጸው ሲሆን የተረት ስፈርን ነዋሪዎች የዕለት ተዕለት ኑሮ በከተማ ቤት አዋጅ ምክንያት የተፈጠረውን ችግር በመዘርዘር በሀገሪቱ የሰፈነውን ማህበራዊ ውድቀት ያወጋበት መፅሀፍ ነው።

ደራሲው

1 -በጋሀዱ ዓለመና በተስፋ ዓለም መካከል ያለውን ልዩነት አጉልቶ የሚያሳይ

2-ሰፊ ያስተሳሰብ ለዩነት በማህበረሰቡ ውስጥ እንዳለና መንኛውም ለውጥ ከዚህ አስታሳሰብ መመንጨት እንዳለበት የሚጠቁም

3-የሀገሪቱን የኑሮንና የኢኮኖሚ ውድቀት የማህበረሰቡን የዕለት ተዕለት ህይወት በመኖር እንድናየው ያደረገበት

4-በሀገሪቱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚ አቅጣጫ ላይ የማረምና የማስተማር አቀራረብ የሚታይበት

5-በጊዜው የነበረው ስርዕት ከእራሱ አስተሳሰብ ጋር እንደሚጋጭ ያጋለጠበት

7 የመናገር ፤ የመጻፍ ፤ የማንበብ ነዓነት ከግል ነፃነት እንዴት እንደሚነፃፀር ያስተማረበትና በወቅቱ ጸሀፊያን ያለባቸውን ችግሮች በሰፊው የሚያትትበት ነው።

ኦሮማይ

ንግግር ፤ ንግግር ብዙ ንግገር ትንሽ ስራ ግምገማ ፤ ግምገማ ብዙ ግምገማ ትንሽ ውጤት ፤ መፈክር ፤መፈክር

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ነጋ ጠባ ዘመቻ እድገት በህብረት ብሎ ዘመቻ ፤ ለጦርነት ዘመቻ ፤ የኢኮኖሚ ግንባታ ዘመቻ ፤ ማህይምነት ለማጥፋት ዘመቻ ፤ የቁጥጥር ዘመቻ ፤ አሁን ደግሞ የኤርትራን ችግር ለመፍታት ዘመቻ

ነጋ ጠባ ስብሰባ ፤ ጠዋት ስብሰባ ፤ ማታ ስብሰባ ፤ የማያቋርጥ የስብሰባ ህይወት

የኢትዮጲያ ችግር ሁሉ ባአዋጅና በዘመቻ እንደ በጋ ጉም በኖ የሚጠፉ ይምስላቸዋል መሰረታዊ ችግራችን የአይምሮ ድህነት መሆኑን ያዋጅ ፤ የማጠናቀሪያ አዋጅ ጋጋታ ፤ ዘመቻ ብሎ ጭጭታ ትርምስ መተራመስ ተተራመሶ መሞት በማለት በጊዜው በጥናትና በዝግጅት ላይ ያልተመሰረተው የሀገሪቱ ሀብት በተገበረበት በቀይ ኮከብ ዘመቻ የማስታወቂያ ሚኒስትሩ ተወካይ ፀጋዬ ሀይለማሪያም ታሪክ ላይ ያነጣጠረውና የታሪኩ ተራኪ እራሱ ደራሲው መሆኑን በየምዕራፉ እያስተዋወቀ በደራሲው በእውን የታየው ፤ የተደረሰውና የተተረከው ኦሮማይ በኢትዮጲያ ታሪክ  ታሪካዊና ህይወትን መሳይ ድንቅ ነገር የተሰዋበት ድንቅ መዕሀፍ ነው። በዚህ መፅሀፍ በጊዜው የነበረውን የኤርትራን ችግር  ፤ሴቶችን በመድፈር፤ ካለመንም ፍርድ የሞት ቅጣት በመፈፀም ፤ ወጣቱን በማስበርገግ የብህራዊ ጦር ፤ የ15ኛ ብርጌድ ፤ ህብረት ዕዝ ፤ ከደርግ ምርመራ አፋኝ ጓድ  ፤ የህዝብ ድርጅት ጊዚያዊ ጽህፈት ቤት የመሳሰሉ ቡድኖች ለችግሩ መባባስ ምክንያት እንደሆኑ በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን

ውታደሩ ከአመራሩ በተለየ መልኩ ሀገሩን የሚወድ ለሀገሩም የተሰዋ ቢሆንም ጦርነቱ ፖለቲካዊ መፍትሄ ያልተፈለገበትና አዝማቾቹም ከሀገራቸው ይልቅ እራሳቸውን የሚወዱ ችሎታውና ብቃት የሌላቸው ለጦርነቱም የነበራቸው አመለካከት በጣም የቀለለ የኤርትራም ህዝብ በባለስልጣኖች በደረሰበት ስቃይ ከሻቢያ ጋር ለማበር መገደዱን ሀገሪቱም የማትችለው ጦርነት ላይ መዘፈቋን አስቀምጧል።

የወቅቱን ባለስልጣኖች በገፀባህሬ መልክ በመሳል እውነተኛ ማንነታቸውን ፤ ልግል ጥቀማቸው የሚያደርጉትን መሯሯጥ ፤ ለስልጣን ያላቸውን ጥም ለጦርነት ሳይሆን ባአስመራ ሴቶች ላይ ለመዝመት የመጡ ዝሙተኞች እንደነበሩ በድፍረት ፅፎታል።

የፍጻሜ መጅምሪያ

በበዓሉ ግርማ በግዜው በማስታወቂያ ሚንስተር ይታተም በነበርው የካቲት ምዕሂት ላይ ብቸኛ የታተም አንስተኛ መጻጻፍ ሲሆን የታሪኩ ገፀባህሬ ህሊና

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

የሚባል ሰው ሲሆን ህሊና ጠጪና ስለ ዕውነት ና ሀቀ ኝነት ለመጻፍ ከእራሱ ጋር በሚያደርገው ትግል ስለነበረው ተስፋና ሰስለነበረበት ፍርሀትነና በጊዜው ሰለ መሰወሩ በኋላም ተመልሰው የሚያደርጉትን ጭውውት የሚተርክ ሲሆን መፅሀፉ በዓሉ ግርማ ክህሊናው ጋር ተመልሶ እንደተገናኘና ከህሊናው ጋር በመታረቂ መሰወሩንና የሚደርስበትን ለመቀበል መዘጋጀቱን የነገረን ዘዴ ሊሆን እንደሚችል ጽሁፉን ያነበቡ ሁሉ ይገምታሉ።

በአድማስ ባሻገር

ጊዜው አላለፈም ይህይወትን ጥሪን ካወቅ ዘንድ ላአንድ ቀን እንኳን እራስህን ግልጽ

በህልና ደውል

ስለችግርና ስለ ብቸኝነት  ለመዝፍን ፍላጎት የለኝም መጻፍ የምፈልገው ስለ ዓለም ውበትና ስለሰው ተፈጥሮ መሰረታዊ ጥሩነት እንዲሁም ሰው በራሱ የራሱን ደህንነት እንዳያገኝ ስለሚያደናቅፉት አካባቢዎች ነው።

በቀይ ኮከብ ጥሪ

ያለ ድርስት ሌላ ህይወት የለኝም ምኞቴ በድርሰት ለሰው ልጅ ደስታን ለማስገኘት ነበር ግን ለሰው ልጅ ደስታን ለመስጠት አልቻልኩም ለራሴም ደስታ አላገኘሁም ስለዚህ የመኖር ትርጉሙ አልታየኝም ባዶነት ይሰማኛል ባዶነትን ፍጹም የሚያደርገው ደግሞ ሞት ነው ፍጹም መሆን አለበኝ

በሀዲስ

እኔ የምወደው በሰው ልብ ተሰፋ ፍቅርና ቆራጥነት የሚያጠናቅር ውበት ያለው ቅኔ ነው።

በደራሲው

እኔ የምጽፈው ስለ ልበ ሙሉነት ስለ ድፍረት ነው

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ድፍረት ለሌለው ብዕር ወረቀት ባታበላሹ ይሻላል
የሰው አካለና ነፊስ አንደ ስለሆነ የሚጸድቀውም የሚኮነነውም በራሱ ልብ ውስጥ ነው።

በኦሮማይ
 የሚሞትበትን የሚያውቅ ማን አለ? በነፃነት ኖሮ በነፃነት ሞሞት የሻላል።

ብዕሩ ዕውነትን ለመግለፅ በትግል ላይ እንደነበረች ፤ ስሜቱ ሰው ከማንም በላይ ክቡር መሆኑን እንደገለጸች ፤ ምኞቱ በብዕሩ ለወገኖቹ ደስታን መቸር መሆኑን ፤የድርሰት ፍቅሩ የልክፍት ያህል ከድርስት እንደተቃራኘ መኖሩን ደፋርና አዋቂ ታላቅ የስንዕሁፍ ሰው እንደነበረ በፁሁፎቹ ከእውነትና ክድርሰት ሊለየው የሚችል ሞት ብቻ እንደነበር ይህንንም ለመቀበል ዝግጁ መሆኑን ብብዕር ውጤቶቹ ቁልጭ አድርጎ ያሳየን ታዋቂው ደራሲ ዛሬ በህይወት ቢኖር ብዙ ስራዎችን ሊያካፍለን ይችል የነበረ ሲሆን

የበርካታ ሰማዕታት አሟሟት ሚስጥር ሲገለጽ

የንጉሱ አፅም ከኮ/መንግስቱ ሐ/ማርያም ቢሮ ስር ተቆፍሮ ሲወጣ

የ60ዎቹ የንጉሱ ባለስልጣኖች አፅም ከአዲሰ አበባ ከርቸሌ በፍለጋ ሲለቀም

የእነ አቡነ ቴዎፋለዎስ አፅም ክልዑል አስራተ ካሳ መኖሪያ ግቢ ውስጥ በቁፋሮ ሲገኝ

በዓሉ ግርማ የት ገባ

በመጭረሻ ለበርካታ ደራሲ በዓሉ ግርማን ለበርካታ ዓመታት መለስ ያላገኙትን ቤተሰቦቹን በተለይም ባሌቤቱንና ልጆቹን ለአንድ ደቂቃ በህሊና ጸሎት እንድናስባቸው እንጠይቃለን

created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional